# የትግራይ በጠላት እጅ መውደቅና
# በኢትዮጵያ ያስከተለው መዘዝ (ክፍል ሁለት)

ከገብረመድህን አረአያ
(ኤዲተር - መላኩ ፀጋዬ መኮንን)

ባለፈው ክፍል አንድ ዝግጅቴ ወደ ሱዳን የገባው ስደተኛ የሚሰጠውን እርዳታ በተመለከተ በድርቅ የተጎዳው ሕዝብ የተለገሰው መጠነ ሰፊ እርዳታ የወያኔ አመራር የፈጸመውን አሳፋሪ ተግባር ሳልገልጽ በማንጠልጠል በይደር አሸጋገሬው ነበር። ወቅቱ የማርክሲስት ሌኒኒስት ሊግ ትግራይ (የማሌሊት) ምስረታ ስለነበር በቅድሚያ ስለሊጉ ምስረታ ከመሰረታዊ ጉዳዩ ጋር የተቆራኘ በመሆኑ ትንሽ ላውጋችሁ።

ለአንባቢዎቸ የማሳስበው የዚሁ የማ.ሌ.ሊ.ት ጉባኤ ጠቅላላ ከአዳራሹ ሥራ እስከ ጉባኤው መጠናቀቂያ የወጣውን ሂሳብ የሰራሁት እኔ ራሴ ነኝ ። በወቅቱ የህ.ወ.ሓ.ት የፋይናንስ ሃላፊ ስለነበርኩ ምስክርነቴን በሰፊው የምሰጠው ከዚህ እውነታ በመነሳት መሆኑን እንድትገነዘቡልኝ እጠይቃለሁ።

## 1977 ዓ.ም የማ.ሌ.ሊ.ት.ጉባኤ

ጉባኤው ከመግባታችን በፊት የጉባኤው አዳራሽ እንዴት እንደነበረና በስንት ወጪ እንደተሰራ አስቀድሜ ላመልከት፤ የጉባኤ ቦታ ወርዒ ውስጥ ሆኖ አዳራሹን ለመስራት ወታደራዊ ጥናት ተደርጎ ከአይሮፕላን ድብደባ፤ በረጅም ከሚወነጨፍ ሚሳይል ጥቃት ነፃ የሆነና የደርግ እግረኛ ሰራዊት በቀላሉ የማይጥሰው ምሽግ በሀያሎም አርአያና ሌሎች ወታደራዊ አባላት ተጠንቶ አስተማማኝ መሆኑ ከተረጋገጠበት በኃላ ነው የጉባኤው ዝግጅት ተመርጦ ሥራው የቀጠለው።

የጉባኤ አዳራሽ ለመስራት ዋና መሀንዲሱ ታዬ አስገዶም ሲሆን የበላይ ተቆጣጣሪዎቹ ደግሞ ሙሉጌታ አለምሰገድና ሚቼ የደህንነት ሀላፊ ክንፈ ገብረመድን ነበሩ።ሥራውን ከሱዳን የመጡ 120 አናጢዎች ለያንዳንዳቸው በወር 600 ብር ደመወዝ እየተከፈላቸው ለአራት ወራት ሰርተው ሲያጠናቅቁ ለእነርሱ ምግብ አብሳይነት የተቀጠሩ 10 ሴቶች በበኩላቸው 300 ብር በወር ሲከፈላቸው በአጠቃላይ ለአናጢዎቹና ለምግብ አብሳዮቹ 240,000 ብር ተከፍሏል። ለአዳራሹ ሥራ በጠቅላላ አራት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሽህ ብር የወጣ ሲሆን 500 እንግዶችን እንዲይዝ ተደርጎ የተሰራ ነው። አዳራሹ ጣሪያውና ግድግዳው በቀይ ጨርቅ ተሸፍኖ በፍሬም የማርክስ፣የሌኒንና የእስታሊን ምስሎች ብሎም ማጭድ፣መዶሻና ኮከብ ያሉበት በብጫ ቀለም እና ብልጭ ድርግም በሚሉ መብራቶች በማሸብረቁ ለተመልካች በሌሊት የሰለጠነች ከተማ ይመስል ነበር። አዳራሹ ኤሌክትሪክ የሚያገኘው በሰዋራ ቦታ በተቀመጡ ጀኔሬተሮች አማካኝነት ሲሆን ለአዳራሹ ማስዋቢያ ከተገዙት እቃወች መካከል በርካታ ረጃጅም ጣውላዎች፣ባህርዛፎች 250 የፕላስቲክ ጥቅሎች፣1000 ጣቃ ጨርቅ፣1500 ጣቃ ቀይ ቀለም የተቀባ ጨርቅ ይገኙበታል።

## <u>ጉባኤው</u>

ጉባኤው ያሰባሰበው የሰው ብዛት ከፈተኛ ነበር።በዚሁ መሰረት፤

| | |
|---|---|
| በጉባኤው በሙሉ ድምፅ የሚሳተፉ | 250 |
| ካለድምፅ የሚሳተፉ እንደነ ተፈራ ዋልዋ፣ ታምራት ላይኔ፤ አዲሱ ለገሰ፤ | 120 |
| አራት ብርጌድ ጥበቃ የሚያካሂዱ | 6, 520 |
| ሬዲዮ ኦፕሬተር ሌላም ተጨምሮ | 450 |
| በካድሬ ትምህርት የነበሩ ሰልጣኞች | 350 |
| የምግብ ስራተኛ በደመወዝ የሚሰሩ | 200 |
| በሐስን ሽፋ የሚመራ ሀለዋ ወያኔ ልዩ ኃይል | 80 |
| በጠቅላላው ድምር | 7970 |

ጉባኤው ሀምሌ 5 ቀን 1977 ዓ.ም ከጠዋቱ ሶስት ሰአት ሥራውን ጀመረ። የአድራሹ ሁለት በሮች ተከፈቱ፣ በጣም አሸብራቂና ልዩ ነበር፣ የማናውቀው ገነት የገባን እንጂ በሰው የተሰራ አይመስልም። በጉባኤው ፊት ለፊት በአማረ መልክ የተሰራ ሙሉውን በቀይ ጨርቅ የተሸፈነ የኮሚኒስት አርማ ይታያል፡ ከቀኝ ወደግራ ማርክስ፣ ሌኒን እስታሊን በትልቅ ፍሬም ሆነው ይታያሉ።የስብሰባው መሪዎች ትልቅ ጠረጴዛ በቀይ ጨርቅ ያጌጤ የህ.ወ.ሓ.ት ባንዴራ አለው። አስራ አንድ ወንበሮች ፊት ለፊት አስራ አንድ የድምጽ ማጉያዎች (ማይክራፎኖች) ተደቅነዋል።፣ በትንሽ ፍሬም የተሰራ የነማርክስ የሶስቱ ስእሎች በጠረጴዛው ፊትም ይታያሉ።

በጉባኤው ላይ  የኢ.ህ.ዲ.ን አባላትና የሻቢያ አባላት ከታጋዩ ተደባልቀው በመሳተፍ ላይ ናቸው። በስብሰባው ድምፅ የሚሰጡና ካለድምፅ የሚካፈሉ በገመድ አጥር ተለይተዋል። በሩ ተከፍቶ ከትንሽ ደቂቃዎች በኃላ ስዩም መስፍን ወደ መድረክ ወቶ  እንኳን ደህና መጣችሁ የሚል በቁራጭ ወረቀት የተፃፈውን መልክት አነበበ።

በመቀጠልም የፕሬዚዲየም አባላት አንድ በአንድ በስብሀት ነጋ ተጠርተው ወደ መድረኩ እየመጡ በተዘጋጀው ወንበር ተቀመጡ። በዚሁ መሰረት፣1. መለስ ዜናዊ
2. ስብሀት ነጋ 3. አባይ ፀሀይ 4. ስዩም መስፍን 5. ተወልደ ወ/ማርያም 6. ገበሩ   አስራት 7. አርከበ እቁባይ 8. ስዩ አብርሃ 9. ግደይ ዘራፂዮን 10. አርጋዊ በርሄ 11. አርጋሽ አደነ በየቦታቸው ተቀመጡ። በሊቀመንበርነት ጉባኤውን የሚመራው ስዩም መስፍን ነበር። የጉባኤው ስብስባ ቀጠለ ትልቁ አጀንዳው ማርክስ ሌኒናዊ ርእዩተዓለም ማእከል ያደረገ መርህ መቀበላቸውንና  የህ.ወ.ሓ.ት. አመራር ሁሉ ማርክሲዝም ሌኒናዊ መሆኑን በማረጋገጥ በሞቀ ጭብጨባና ደስታ ቀጠለ፣ሌላኘው አጀንዳ ድግሞ የድርጅቱ ፓሊሲ በተመለከተ ሲሆን በ1ኛው ጉባኤ የወጣ ፖሊሲ በ2ኛ ጉባኤው ይፀናል፡ ይዘነው በመጣነው ፓሊሲ ሳይለወጥ ሳይቀነስ ይቀጥላል ተብሎ በሙሉ ድምፅ ፀደቀ።

ቀጥሎ የመጣው የማእከላይ ኮሚቴ ምርጫ ነበር ማ/ኮሚቴ በእለቱ ከመረጡት 25 አባላት መካከል አረጋዊ በርሄና ግደይ ዘራፅዮን ይገኙበታል፡ የፖሊት ቢሮን ምርጫ ለቀጣዬ ቀን ተቀጥሮ የእለቱ ውሎ ተጠናቀቀ። በሁለተኛው ቀን ስብሰባው እንደተጀመረ ስብሀት ነጋ ተነስቶ “ግደይ ዘረአፅዮን የቡርዥው ርእየተአለም ተከታይ ነው፣ በመሆኑም ከማ.ሌ.ሊ.ት መርህ ጋር ሊጓዝ አይችልም ረግረግ ውስጥ ገብቶ የሰጠመ ነው፡ በፖሊሲም ልዩነት ባይኖረን አሁን አሮጌ እቃ ነው። ከዚሁ ተነስተን ከህ.ወ.ሓ.ት.እና ከማ.ሌ.ሊ.ት. ተወግዷል። ወደፈለገው መሄድ ይችላል፣ የድርጅቱን ዶኮሜንትና ንብረት አሁን እንረከባለን አለ።” በመቀጠልም ሁለተኛው ተባራሪ ደግሞ ሲያስተዋውቅ “አርጋዊ በርሄ በፓሊሲ ልዩነት የለንም። ግን ጠቃሚ ነው ብለን እምነት ስለሌለን ከአሁኑ ጀምሮ ያለውን የድርጅቱ ንብረት ያስረክበናል፤ ወደፈለገበት ሀገር ለመሄድ ይችላል” ሲል አወጀ። በመቀጠልም መለስና ስብሀት በእጃቸው የነበረውን የድርጅቱን ንብረት ተረከቡ። ወደ ጉባኤ አዳራሹ እንዳይገቡ ታገዱ። ከሰአታት በኃላ የማእከላዊ ኮሚቴ አባልነታቸውን ቦታ ለቀው እኛ ወደምንኖርበት አካባቢ ተቀላቀሉ። ሁለቱም የተባረሩት በስልጣን ሹኩቻ ብቻ ነው ምንም ነገር ጠብና አለመግባባትም አልነበረባቸወም አሁንም በተለይ አረጋዊ ብርሄ መለስ ዜናዊን ይደግፋል።የተባረሩትን ሁለት ታጋዮች አስመልክቶ በትንሹ ለመግለጽ በአረጋዊ በርሄ መባረር ሁሉ ተጋይ ስሜትም አልሰጠውም ነበር። በግደይ ዘራፅዩን መባረር ግን በጉባኤው ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው ብዙ ታጋይ ነበር ያዘነው። በመጠኑም ቢሆን በተለያዩ ጊዜም የታጋይ ግደይ በሕንፍሽፍሽ የተከላከለበት ጊዜ ነበር። የማጽዳት ዘመቻ ተብሎ ብዙ ታጋይ ሲገደል በመሃል ገብቶ ግድያውን ያቆመው ግደይ እራሱ ነበር።

ወደ ስብሰባው ሂደት ልመልሳችሁና ከዚህ በኋላ የቀረበው  የማ.ሌ.ሊ.ት ፓሊት ቢሮ ተሿሚዎች ዝርዝር ሲሆን በዚሁ መሰረት 1 ስብአት ነጋ፣ 2 መለስ ዜናዊ፣ 3 አባይ ፀሃዬ፣ 4 ስዩም መስፍን፣ 5 አውሎአለም ወልዱ፣ 6 ገብሩ አስራት፣ 7 ስዩ አብርሀ፣ 8 ተወለደ ወ/ማርያም፣ 9 ፃድቃን ገ/ትንሳኤ ሙሉ አባልነት ሲሾሙ ተለዋጭ ፓሊት ቢሮ አባላት ደግሞ አርከበ እቁባይ እና አረጋሽ አዳነ ሆኑ። እነዚህ ሁሉ የመለስና ስብሃት ታማኞች ናቸው።

ይህ ጉባኤ የተካሄደው የትግራይ ህዝብ በድርቅ ምክንያት እንደቅጠል እየረገፈ ባለበት ወቅት ነው። የጉባኤው ወጭም ከዚሁ ሕዝብ የተነጠቀ ሃብት ነው። የሰው ልጅ እየረገፈ በየመንገዱ ቀባሪ አጥቶ የጅብ ቀለብ በሆነበት ወቅት ነው ስብሰባው ለ15 ቀናት የተካሄደው።የጉባኤውን ቆይታ ወጭ ለትዝብት እንመልከት፣ የምግብና መጠጥ ለትዝብት እንመልከት። በማእከላዊ ኮሚቴ የምግብ ዋና ሃላፊ ወ/ሮ ኤልሳ አስፍሃ የፃድቃን ገ/ጻዲቅ ሚስት ስትሆን በእሷ እዝ፣ስር በቅደመ ዝግጅቱ  300 ከብቶች ለእርድ ቀርበዋል። በየቀኑ ከ7-10 ከብቶች እና ሁለት ፍየሎች ይታረዳሉ፡ ሁሉ ጉባኤተኛ የሚመገበው የነጭ የጤፍ እንጀራ ነው፣በየቀኑ ጠዋት ቁርስ አምባሻና ስጋ ጥብስ ሆኖ ምሳ፣እና እራት ቀይ የስጋ ወጥ፣ አልጫ የስጋ ወጥ፣ ጥብስ ይቀርባል፡ በተጨማሪም የታሸጉ

ፍራፍሬዎች እና አትክልት እንደ ልብ ነው፡ መጠጥ ጠጅ፣ ጉሽ ጠላ፣ የጠራ ጠላ እንደውሃ ይንቆረቆራል፣ እንደዚሁም ዊስኪና ቢራ በጅምላ ነው።

የጉባኤው ተሳታፊዎች አብዛኞቹ የተገኙት ከነሚስቶቻቸው በመሆኑ ምርጥ ፍራሽ፣ ብርድ ልብስና አንሶላ ከሱዳን ተገዝቶ እየተንፈላሰሱ ናቸው። በዚሁ መሰረት በቀን የሚወጣው ወጪ እንኳንስ ሽምቅ ተዋጊ ቀርቶ የአንድ ሃብታም ሀገር መንግስትም ሊያወጣው የማይችል ነበር። በጣም ከፍተኛ የገንዘብ ውጭ ነበር የተደረገው ቀን በጉባኤው እየዋልኩ ማታ ማታ ሂሳቡን እየሰራሁ ለረዳቴ ኃይለ ሊባኖስ እሰጠዋለሁ። የእሱ የእጅ ጽሁፍ በጣም ጥሩ ስለሆነ በሶስት ኮፒ እያዘጋጀ ይጽፋል፡ በጥቅሉ የሂሳቡ ሰንጠረዥ ከ50 ገጽ በላይ ሲሆን ባጭሩ የወጭው ዝርዝር ለግንዛቤ እነሆ፣

| | |
|---|---|
| ሀ) ለምግብ፣ ለመጠጥ፤ ለስጋ ጠቅላላ ወጭ | 28,000,000 |
| ለ) ለጉባኤው አዳራሽ ማሰሪያና ለተለያዩ እቃዎች መግዛ | 4,700,000 |
| ሐ) ለጄነረተርና ለሌሎች ቁሳቁሶች የወጣ ወጭ | 1,500,000 |
| መ) ለተለያዩ እቃዎች መግዥ የወጣ ወጭ | 2,332,000 |
| ጠቅላላ ድምር | 36,532,000 ብር |

በአጠቃላይ  ሰላሳ ስድስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሰላሣ ሁለት ሺህ ብር ወጭ በማድረግ የህ.ወ.ሓ.ት. መሪዎች ተሞሽረው ወጡ። የጉባኤው ሁኔታ በዚሁ ላብቃና አቋርጬ ወደ ተወኩት ቁም ነገር ልመለስ።

እነሱ በዚህ ሁኔታ ላይ ሲምነሸነሹ በስደተኞች ጣብያ አስገድደው ያጎሩትን  ሕዝብ የህ.ወ.ሓ.ት.ማ.ሌ.ሊ.ት. አመራር ምን አይነት የቀለብ ራሽን ያደርግላቸው እንደነበር ቀድሞ ብየ እንደገለፅኩት ጥሬ በቆሎ እና ባቄላ ነበር።  ለዚያውም 10 ኪሎ ገደማ ሲሆን የተፈቀደላቸውም ቆልተው ብቻ እንዲበሉ በሚያስችል መቁንን ገድበውታል። በህክምና ረገድ በጣም የተጎዱ ነበሩ። በየቀኑ በበሽታ ምክንያት ሕዝብ እያለቀ እየሞተ ነው። በሐምሌ ወር 1978 ዓ.ም  አጥጋቢ ዝናብ መጣሉን የተረዱት ረሀብተኞች ውስጥ ለውስጥ በመላላክ  ወደ ኢትዮጵያ ያጠራቀሙትን በቆሎ፣ ባቄላና ጨው ይዘው የስደት ካንፑን አጥር ሰብረው ወጡ። ደህና አቋም ያለው ሌትም ቀንም እየተጓዘ ወደ ትውልድ ቀበሌው ደረሰ፣የታመሙት ብቻ በስደት ጣቢያዎች ቀሩ እነሱም ካገገሙ በኋላ አጥሩን እየገፈተሩ ሄዱ፡ የተወሰኑት ወደ ሱዳን ካርቱም ሲያቀኑ ቀሪዎቹ ደግሞ ወደ ወልቃይት ጠገዴ ተጓዙ፤ በሚገባ ከጠነከሩ በኃላ ወደየቦታቸው ተመለሱ።

## የማ.ሌ.ሊ.ት.ዋና መናሃሪያ (ቤዝ)  ደጀና እንዲሆን ተወሰነ

ማ.ሌ.ሊ.ት. እንደተመሰረተ ዋና ጽ/ቤቶች ደጀና እንዲሆን በመወሰኑ በተሰጠን መመሪያ መሰረት ደጀና ገባን በዚሁ ቦታ፣ ፕሮፖጋንዳና ከሕትመት ክፍል መለስ ዜናዊና አባይ ፀሀዬ፤ ማህበራዊና ኢኮኖሚ ጽ/ቤት ገብሩ አስራት፤ ወታደረዊ ጽ/ቤት ስዩ አብረሃ የውጭ ጉዳይ ቢሮ ስዩም መስፍን የሚመሩት ቢሮ በየክፍሉ ተደራጀና ሰራውም ቀጠለ። ደጀና የተመረጠበት ዋና ምክንያት ከአንገረብ ተሸግሮ በቀጥታ ሱዳን ስለሚያስገባና የሚመጣው እህልና ንብረት ከሱዳን ካለምንም ችግር ወደ ደጀና ስለሚደርስ በስልታዊ አቀማመጡ ጭምር ነው። አሁን በድርቅ ከተጎዳው ሕዝብ በተዘረፈ ንብረት ወያኔ ህ.ወ.ሓ.ት.. ማ.ሌ.ሊ.ት ፍጹም ሀብታምና ባለፀጋ ለመሆን በቃ።

ይኸንኑ አትራፊ ተግባራቸውን በመቀጠል በረሃብና በበሽታ አጥንቱ ብቻ ተሸክሞ የሚንከላዎሰውን መከረኛ የትግራይ ህብረተሰብ በየቴሊቭዥኑ ለአለም ህብረተሰብ ጎስቋላ አካሉን እያሳዩ የሚሰጠው እርዳታ ለተጎጅው የሚደርስ የመሰላቸው ለጋሾች እና ሰብአዊ ስሜት የተነሳሳው የዓለም ሕብረተሰብ ከእኔ  ይቅርብኝ ብሎ ለግብረሰናይ ድርጅቶች ማለትም OXFAM, Save the Children, US Aid, Red cross, Care International, World Vision, Red Crescent, U.N humanitarian team ለመሳሰሉት እርዳታውን እንዲያደርሱለት ሰጠ። በአለም አቀፍ መሪነቱን የያዙት የመገናኛ ብዙሀን  B.B.C, CNN, CBS  ወዘተ የመሳሰሉት ሳይቀሩ የረሀቡን አስከፊ ደረጃ ወኪሎቻቸውን ቦታው ድረስ በመላክ ከፍተኛ ሽፋን ሰጡ። የአለም ከያኒያን ከአህጉር አህጉር ተጠራርተው የበኩላቸውን የገንዘብ መዋጮ በማሰባሰብ ታሪካዊ ድርሻቸውን ተወጡ። አለም የደረቀ ጉሮሮን ለማራስ የታጠፈ አንጀትን ለማቃናት ሲረባረብ ከአብራኩ ወጥተናል የሚሉት ስብሃት ነጋና መለስ ዜናዊ የሙት ተስካራቸውን ለሙብላት የበኩላቸውን  የዘረፋ መዋቅር በከፍተኛ ደረጃ አዘጋጁ።

የወያኔ መሪዎች ለህዝብ ተብሎ የመጣውን እርዳታ ወደ እነሱ ጥቅም ስለለወጡት የእህል ማመላለስ እቅድ አወጡ። በዚሁ መሰረት በከባድ የጭነት መኪናዎች ተመድበው ከአንገረብ ጀምሮ በየቦታው የአንድ ኪሎ

ሜትር ርቀት ክፍተት በመተው በየነቁጡ ጣቢያ በታች ድንጋይ በማንጠፍ እላዬ እንጨት እየተረበረበ 30,000 ሺህ ኩንታል እህል በአንድ ቦታ እንዲከመር ተደረገ። በዚህ እረገድ ከአንገረብ እስከ ተከዜ ድረስ 1000ሺህ ክምር ተከማቸ። ይህ የስንዴ ድቄት ስኳር ወተት ቅባት ብስኩት ሻይ ቅጠል ወ.ዘ.ተ.ሆኖ ላስቲክ ከላይ እስከታች እየተሸፈነ በየዱር ትልልቅ ዛፎች ስር እየተደበቀ፡ በሌላው ዘርፍ ደግሞ አሁንም በተመሳሳይ ሁኔታ ከተከዜ እንደባጉና ድረስ 700 ክምር ተደራጀ በተለይ ሽራሮ፣አዲ ሀገራይ፣ አዲ አውአላ፣ አዲነብረኢድ ቀደም ሲል የኢዲዩ አባላት የነበሩና ንብረታቸውን ተነጥቀው የተባረሩ ባለሀብቶች ያሰሩአቸው ሰፋፊ መጋዝናች ውስጥ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ተጠራቀመ፡። ይህ ለወያኔ ትልቅ አፎይታ ሰጠው። በወያኔ አመራር እቅድ መሰረት የአምስት አመት ለሰራዊት ምግብ እንዲሆን ተዘጋጀ።በባዶ አምስት ክፍለ ኢኮኖሚ አከፋፋይነት ተዋጊው የሚፈልገውን የምግብ አቅርቦት ያገኛል ከዚህ ጀምሮ ሰራዊቱ የቀን ወጪው ብር 14 እንዲሆን ተመደበ።

ሌላው አሰቃቂ ድራማ ደግሞ የተከሰተው ደጀና እንደገባን በሰር ቦብ ጎልዶፍ / Sir Bob Goldof / የሚመራ ባንድ ኤድ / BAND AID / ተብሎ የሚጠራው የኪነት ቡድን ለስዩም መስፍን ድብዳቤ በመላክ በድርቅ ለተጎዱ የእርዳታ ገንዘብ ለመስጠት እንደሚፈልጉና በህወሓት በኩል ተረክበው ለማከፋፈል እንዲቻል ግንኙነት የሚደረግበትን ሁኔታ የሚገልጽ ደብዳቤ ደረሰው። ስዩም ደብዳቤውን ተረክቦ ለስብሀትና ለመለስ ነገራቸው፡ በመቀጠል የት ሃገር እንደሚሄዱ ካዘጋጁ በኃላ አስቀድሞ ስብሀት ነጋ ወደ ሱዳን ሄደ፣ ቀጥሎ በሁለኛ ቀኑ መለስ ዜናዊ ተነስቶ ወደ ሱዳን ተጓዘ። ሁለቱ ሱዳን ከተገናኙ በኃላ የኪነት ባንዱን ከሚያገኙበት ሀገር ድረስ ሄዱ። ከባንድ ኤድ U.S dollars $100,000,000 (አንድ መቶ ሚሊዮን) ዶላር ሁለቱ ፈርመው ከተቀበሉ በኃላ ገንዘቡን በግል የባንክ አካውንት ለሁለት ተካፍለው አስቀምጠው ባዶ እጃቸውን ተመለሱ። ከሱዳን ሲመለሱም ቀድሞ ስብሀት ነጋ ወደ ደጀና ተመለሰ። በሶስተኛው ቀን መለስ ዜናዊ መጣ። ይህን ጉዳይ ለማወቅ የቻልኩበትን ምክንያት ባጭሩ ልግለጥላችሁ። ነገሩ እንዲህ ሆነ። ገብሩ አስራት የኢኮኖሚ ጉዳይ ሀላፊ ስለሆነ ጉዳዩ ይመለከተዋል በሚል አባይ ፀሃዬ በስህተት ድብዳቤውን ፎቶ ኮፒ አመጣና ሰጠው። ገብሩ አስራትም እኔን አስጠራና ይኸው ይህ ገንዘብ በባንድ ኤድ የተሰጠው በድርቅ ለተጠቃው ለትግራይ ህዝብ ማቋቋሚያ ስለሆነ ገንዘቡ ወደ ኢትዮጵያ ብር ተለወጦ ለህዝቡ በእርዳታ እንድታከፋፍሉ አደራ እንላለን የሚል ነበር። ከአነበብኩት በኃላ አስቀመጥኩት። አባይ ተመልሶ ደብዳቤውን የሰጠው በስህተት መሆኑ አምኖ በአስቸኳይ ደብዳቤውን እንዲመልስ መልክተኛ ለገብሩ ላከበት ገብሩ አስራትም ከእኔ ተቀብሎ መለሰለት፡ ሚስጢሩ ያወኩት በዚህ የተነሳ ነው።

## የጉና የንግድ ድርጅት መቋቋም

ጉና ተብሎ የተሰየመው የንግድ ድርጅት የተቋቋመው ከአለማቀፍ ህብረተሰብ በእርዳታ የተገኘውን ንብረት ለመሸጥ እና ለማ.ሌ.ሊ.ት.ቀይ ሰራዊት ከአራት እስከ አምስት አመት የስንቅ ክምችት ለማስቀመጥ እንዲያስችል በመጋቢት 1978 ዓ.ም ነው። መስከረም 1978 ዓ.ም ፖሊት ቢሮው ክሳድ ግመል በተባለ ቦታ ተሰብስቦ በድርቅ የተጎዳ ሕዝብ የተሰጠውን እርዳታ በግልጽ ለመዝረፍ ውሳኔ የሰጠበት ወቅት ነው። በውሳኔው መሰረት ከእርዳታ የሚሰበሰበው ንብረት በሚከተለው ሁኔታ ሸነሸነው፣

1. ለማርክሳዊ ሌኒናዊ ሊግ ትግራይ /ማ.ሌ.ሊ.ት./ ማጠናከሪያ 55%
2. ለቀይ ሰራዊት 45%
3. ለህዝብ እርዳታ 5% ክፍፍል እንዲደረግ በሚል

ድልድል ተወሰነ።

በዚሁ አመዳደብ ለህዝብ ብለው ያስቀመጡት 5% ከመቶውን ቢሆን ለማንም አልተሰጠም። ቀደም ሲል እንደገለጽኩት በድርቅ ለተጠቃው ህዝብ ቅንጣት ታክል አልተሰጠም። ለዚሁም የትግራይ ህብረተሰብ ምስክርነቱን ይሰጣል።

በዚሁ ጊዜ ከፓሊት ቢሮው አባላት አንዱ ስዩ አብርሃ "አመራሩ የሚሰራው ስራ ትክክል አለመሆኑን ለህዝብ እርዳታ ተብሎ በሕዝብ ስም ለምነን ያገኘነውን ሩብ ኪሎ እንኳ ለህዝብ አልሰጠንም። ህዝብ በሞት፣ በበሽታ፣ በርሃብ እያለቀ በአይናችን እያየን ይህን አለማድረጋችን ፍፁም ክህደት ፈፀመናል በአሁኑ አመዳደብ አልስማማም አልቀበልም" ብሎ ውሳኔውን መቃወሙን በአመራሩ መካከል ስጋት ፈጥሮ እንደነበር በቅርብ ይህን የሰሙ የማ/ኮሚቴ አባላት ውስጥ ለውስጥ ነገሩን። ስየን ለመግድልም በስብሃትና በመለስ ታቅዶ እንደነበርም ይወራ ነበር። ከግድያው በምን እዳመለጠ የማውቀው ነገር የለም። እኔና ገብሩ አስራት በአንድ ላይ ስለምንሰራ በአንድ ወቅት ስለዚሁ ጉዳይ ጠይቄው ፈገግ ብሎ ማነው የነገረህ አለኝ? እኔም ከነበረ ንገረኝ ስለው አልነበረም ብሎ በደፈናው መለሰልኝ ሁኔታውን በዚሁ አቁመን ወደስራችን ገባን። ከዚሁ ቀጥዬ ድግሞ የጉና ንግድ እንቅስቃሴን

ልዳስ። ጉና ማለት የቦታ ስም ሆኖ በወልቃይት ጸገዴ የሚገኝ የሰራዊት ስንቅ በብዛት የተከማቸበት በተራሮች የተማከለና በትልልቅ ዛፎች የተሸፈነ ሥፍራ ነው። የጉና የንግድ ስምም የተወሰደው ከዚሁ ነው።

የጉና የንግድ እንቅስቃሴ በጥቂት ፓሊት ቢሮ የሚታወቅ ሲሆን የዚሁ ውስጥ ለውስጥ መሸጥ ውሳኔ ሰጭዎቹ ስብሀት፤ መለስ፤ ስዩም፤አባይ እና አርከበ፤ ሆነው በዚሁ ሥራ የተሰማሩት 10 የጭነት መኪናዎችን በሹፌርነት የሚነዱት ግደይ ፎሮ፤ ሙሉ ወዲየኔታ፤ ፀጋይ ጠማለሁ እና አክሊሉ ዓላ ብቻ ሲሆኑ የየለት ተግባሩን የሚያስተባብር ደግም አባዲ ዘሙ ሆኖ እየተዘዋወሩ የተሸጠውን እህልና ልዩ ልዩ ንብረት ገንዘብ የሚረከቡ ብርሃነ ገ/ክርስቶስ፤ ቴድሮስ ሀጎስ፤ጀማይካ፤አዲስ አለም ባለማ፤ተወልደ ዓጋመ፡ ሲሆኑ ሁሉም የህወሓት ማ.ሌ.ሊ.ት.ማእከላዊ ኮሚቴ አባላት ናቸው። ከሱዳን ወደ ገዳሪፍ በማጓጓዙ የተመደቡ የጭነት መኪና ቁጥራቸው 294 ማርቸዲስ ረጃጅም መኪናዎች ሲሆኑ፤ ቀሪ 36 የጭነት መኪናዎች ደግሞ ለህ.ወ.ሓ.ት. ሰራዊት በገዳሪፍ የተከማቸውን እየጫኑ ወደ ትግራይ ያግዛሉ። ቀደም ብለው 26 የጭነት መኪናዎች በመለዋወጫ እቃ እጦት ቁመው የነበሩ ሁሉ ተጠግነው ከፓርት ሱዳን ወደ ገዳሪፍ በመቀጠልም ወደ ትግራይ አመላላሽ ሆነው ሰርተዋል።

በጉናው የንግድ ድርጅት የተመደቡ ካድሬዎች ፀጋዬ ጠማለሁ፤ ግደይ ፎሮ፤አክሊሊ አላ፤ሙሉ ወዲየኔታ፤ ተክለሃይማኖት፤መሀመድ ሙባራክ፤ሮማን ገ/ስላሴ፤ ሕሪቲ መሕረተአብ፤ፍስሃ አፈወርቂ፤ወረደ ገሰሰ፤ሳሙኤል ገ/ማርያም፤ነጋሽ ተከሉ፤ሙብራት በየነ፤ ነጋሽ ኒኖ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱ አስራ አራት የወያኔ አባላት በሱዳን ታላላቅ ከተሞች ተሰማሩ። ለሁሉም ቶዮታ ላንድ ከሩዘር ከነሹፌሩ ተሰጣቸው። በቅድሚያ በእርዳታ የተላኩ የጭነት መኪናዎች ብዙዎቹ የተባበሩት መንግስታት፤ World Food Program (WFP) የሚለው ከነአርማው የተሰጡ በመሆኑ አርማው እየጠፋ ተማሳሳይ ቀለም ተቀቡ።በመቀጠልም ሁሉም የጭነት መኪናዎች የሱዳን የሰሌዳ ቁጥር ተለጠፈባቸው። በመቀጥል ያደረጉት በሱዳን ከተሞች ከፍተኛ የመደለል ችሎታ ያላቸውን ሱዳናዊያን በመቅጠር ከነጋዴዎች ጋር እያገናኙ የእርዳታውን ንብርት መሸጥ ነበር።

ከሽያጩ በተጨማሪ ወያኔ ህ.ወ.ሓ.ት.ም ለሰራዊቱ የሚያስፈልገው ስንቅ መድሀኒት የህክምና መሳሪያ እየተጫነ ገዳሪፍ ከተራገፈ በኃላ ወደ ትግራይ ያስገባሉ፡ በዚህ የዘረፋ ተግባር ዋናዎቹ መሪዎች ብቻ ሳይሆኑ የአባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ እንደሚባለው በዚሁ ሥራ የተሰማሩት ካድሬዎችም በበኩላቸው በድብቅ የሁለት ሶስት ጭነት መኪና ለብቻው በመሸጥ ለሹፌሩ ደግሞ አፍ መዝጊያ አንድ ጭነት እየሸጡ በግል በሚሰጥር ባንክ አካውንት ብዙ ገንዘብ አስቀምጠዋል፡ ከላይ የተጠቀሱት 14 የወያኔ ካድሬዎች በየሁለቱ ሳምንቱ የተገኘውን ገንዘብና ቼክ ለአባዲ ዘሙና ለብርሃነ ገብረክርስቶስ ያስረክባሉ። ቀሪዎች ለስዩም መስፍን ይሰጣሉ። በመጨረሻም ዝርዝር ሂሳቡ ተጠናቅቆ በየሶስት ወሩ ለስብሀት ነጋ ደጀና እየመጡ ያስረከባሉ። አንዳንዶቹ እየተደናበሩ ወደ እኔ እየመጡ ይሰጡኝ ነበር፡ በቀጥታ ለገብሩ እንዲሰጡት ስነግራቸው ገብሩ አስራት በፋንታው ይህ እኔን አይመለከትም ለመለስ ወይም ለስብሀት ነጋ ሰጡዋቸው ብሎ ይመልሳቸዋል። በዚሁ ሂደት ጉና የንግድ ተግባር ቀጠለ። በመካከሉ 1978 ዓ.ም ነሀሴ ወር በፓርት ሱዳን የተከማቸው ገና በበቂ አልመነሳቱ የሱዳን መንግስት ወደቡ ጠበበ አንሱልኝ የሚል ቅሬታ ማሰማት ጀመረ።

በዚሁ ጊዜ ብርሃነ ገ/ክርስቶስና አባዲ ዘሙ ካርቱም ውስጥ የሚኖሩ ሱዳናውያ በአለም አቀፍ ደረጃ የድለላ እውቅና ያላቸውን አራት ደላላዎች በማነጋገር በፓርት ሱዳን ያለውን የእህል ክምር፣ የምግብ ቅባት፤ ስኳር፤ ሻይ ቅጠል፤ ብስኩት የህፃናት አልሚ ምግብ ወ.ዘ.ተ. ዝርዝር ፎቶኮፒ በመስጠት በአረብ ሀገሮች እንዲሸጥ መርከብ ተኮናትረው በግብፅ፤ በሳውዲ አረቢያ፡ በኪዌት እና በዩናይትድ አረብ ኤሚሬትስ ከሚገኙ ካምፓኒዎች ጋር ተስማምተው በትላልቅ መርከቦች እየተጫነ ብርሃነ ገ/ክርስቶስ፡ የማነ ኪዳነ/ ጃማይካ/ እና ቴድሮስ ሃጎስ አብረው በመጓዝ አዲስ አለም ባሌማ በሱዳን ፖርት ቋሚ ሆኖ በመመደብ የሶስቱን ስራ ደርቦ በመስራት በመረከብ ኪራይ እየተጫነ ወደ አረብ ሀገሮች ተሸጋገረ። ቀሪው ለሱዳን ነጋዴዎች ተሸጠ። በሙሉ ሽያጩ በአሜሪካ ዶላር ሲሆን በሽያጩ በቢሊዮን የሚቆጠር ገቢ ተገኘ። ገንዘቡ ግን ወደ አውሮፓና አሜሪካ እንዲቀመጥ ተደረገ፡ የጉና የንግድ ዘረፋ 1979 ዓ.ም. ተጠናቀቀ።

በዘረፋው በትክክል የገባውን የሚያውቁት ስብሀትና መለስ ሲሆኑ ገንዘቡን የተከፋፈሉት ደግሞ ስብሀት ነጋ፤ መለስ ዜናዊ፤ ስዩም መስፍን፤ አርከበ ዕቁባይ፤ ብርሀነ ገ/ክርስቶስ፤ አባዲ ዘሙ፤ጀማይካ በዋናነት ሲሆኑ ከ150 ሚሊዮን ዶላር እስከ 200 ሚሊዮን ዶላር ማግኘታቸው በወቅቱ ይነገር ነበር። አነስተኛ አግኝተዋል የተባለላቸው ቴውድሮስ ሀጎስ፤ አዲስ አለም ባሌማ እና ተወልደ ኢጋመ እስከ አምስት ሚሊዮን የማግኘታቸው ወሬ በስፋት ተሰራጭቶ ነበር። ቀሪዎቹ 14ቱ ታጋዮች በየደረጃቸው ከ$10 እስከ-$5 ሺህ ዶላር ጉርሻ እንደተሰጣቸው ራሳቸው ሲነግሩን ነበር። ይህ ጉርሻ እነሱ በበኩላቸው በድብቅ እየሸጡ ከዘረፉት ገንዘብ ውጭ ማለት ነው።

እንግዲህ በድርቅ ለተጠቃው፤ በርሃብና በበሽታ የተነሳ እየሞቱ ያሉት እናቶች፤ ህፃናት፤ ልጆች የእናታቸውን እጅ ተንተርሰው በየመንገዱ ወደቀው ሲቀሩ የሰው ልጅ ሬሳ ወደቆ የአውሬ መጫወቻ ሆኖ፣ አጥንትና ቆዳው የተጣበቀ ህፃን፣ ሽማግሌ፣ እናት  ካሜራ አንሺ ሲመጣ ብቻ መንገድ መሪ ሆኖ ለአለም ህዝብና መንግስታት እያሳዩ በእነርሱ ስም የመጣው እርዳታ መዝረፍ፤ ማዘረፍ ይህንኑም በራስና በቤተሰብ ስም  በተለያዩ ሃገራት በባንክ ማስቀመጥና ለግል ጥቅም ማዋል ከፍተኛ የወንጀል ወንጀል ብሎም የወንጀሎች ሁሉ ቁንጮ ነው።

ችግረኛውን ሕዝብ ከቦታው አፈናቅለው  በሱዳን ካምፕ አስፍረው እንደ ኤክሲፖ ዘርግተው ከለመኑበት በኃላ በስሙ የመጣውን እርዳርታ መዝረፍ በአለም ታሪክም ታይቶ የሚያውቅ አይመስለኝም። ይህ የሚያሳየው ነገር ቢኖር የወያኔ መሪዎች ፍፁም አረመኔ፤ ጨካኝ ሽፍቶች መሆናቸውን ያስመሰክራል። ከባንድ ኤድ የተሰጠውን $100 ሚሊዮን ዶላር ጨምሮ በአለም ህብረተስብ፤ በተባበሩት መንግስታትና ግብረስናይ ድርጅቶ የተለገሰው እርዳታ በዋናነት መለስ ዜናዊና ስብሀት ነጋ ዘርፈው አዘርፈውታል በህዝቡ ላይ ጭካኔ የተሞላበት አሳፋሪ ተግባር ፈጸመዋል። በነገራችን ላይ ሳልጠቅስ ያለፍኩት ነዳጅን በሚመለከት ወያኔ የሚበቃውን ካስቀመጠ በኃላ ቀሪው ለሱዳን ነጋዴዎች ሸጦታል።

## ለማ.ሌ.ሊ.ት ቀይ ሰራዊት ተብሎ የተከማቸው ምግብ በዝናብ መበላሸት

1979 ዓ.ም አምላክ በህዝቡ ላይ ይቅርታ ያወረደበት ዘመን ነበር ማለት ይቻላል። ከግንቦት ወር 1979 ዓ.ም ጀምሮ ዝናብ በጣም አጥጋቢ በሆነ መልኩ መዝነብ ቀጠለ። መሬት ሁሉ ጨሌ በጨሌ ሆነ፣ዛፍ ለመለመ ሳሩ በሰው ቁመት ደረሰ፤ ከብት፤ ፍየል የቤት እንስሳት ሁሉ ጠገቡ፣ ወፈሩ። በግንቦት በጣለው ዝናብ የጓሮ አትክልት ጎመን ደረሰ፤ አዝመራውም በአማረ መልኩ በቅሎ ገበሬውን የደረስኩልህ ተስፋ ሰጠው።   እሸቱን የሚበላበት ጊዜ ደረሰ ጥቅምትና ታህሳስ 1980 ዓ.ም ጥሩ  ምርት ተገኘ።

በተቃራኒው የ1979 ዓ.ም ዝናብ ክፍኛ ያማረረው ወያኔ ህ.ወ.ሓ.ት መሪዎችን ነበር፡ በየቦታው ተከምሮ የፕላስቲክ ሸራ ተሸፍኖ የነበረው እህል በዝናቡ ሃይለኝነት የተነሳና ቀስበቀስ ወደ እህሉ በመግባቱ ከአንገረብ እስከ ተከዜ የተከማቸው 1000 ክምር አንድ ክምሮ (ከ30,000 ኩንታል) ያላነሰ ያየዘው ክምችት እየተበላሸ መጣ። ግማቱ ሰው ሊያስቀርብ የማይችልበት ደረጃ ላይ ደረሰ። በዚህ ወቅት ስብሀት ነጋ፣ መለስ ዜናዊ፣ አባይ ፀሃዬ እና አርከበ እቁባይ ተሰብስበው ክምሩ እየተዘዋወሩ ጥናት በማደረግ የተበላሸውን የሚያስወግድ ኮሚሽን አቋቋሙ። የኮምሽኑ አባላትም፤

1ኛ ሕቡር ገ/ኪዳን                    የቤዙ ዋና አስተዳዳሪ
2ኛ መድሕን                    ወታደራዊ ጽ/ቤት ፐርስኔል
3ኛ ገ/መድህን አርአያ                    የፋይናንስ ሃላፊ
4ኛ ቢያን ጀቲዊ                    የስንቅና ንብረት ሃላፊ
5ኛ ያይኔ                    በያን ፍትዊ ተባባሪ የነበረ
6ኛ ልጀለም                    ሃኪም
7ኛ መዝገብ          በወታደራዊ ጽ/ቤት የካርታ ጥናት ዋና ሃላፊ ሲሆኑ በሕቡር ገ/ኪዳን መሪነት ለሁላችን የተንቀሳቀሱ ትእዛዝ ደረሰን። በዚሁ መሰረት ስራውን ከአንገረብ ጀምረን ተከዜ ለመድረስ አንድ ወር ሙሉ ወሰደብን፤ በካሄድነው ምርመራም 215 ክምሮች ትል ፈጥረው በዝናብ ተጨማልቀው ተገኙ። የተባላሹት በአስቸኳይ ወደ ወንዝ እንዲጣሉ ተወሰነ። ሌሎች 75 ክምሮች መጠነኛ መበላሸት ደርሶባቸዋል። እነዚህም በአስቸኳይ ካልተለዩ  በአጭር ጊዜ ከጥቅም ወጭ እንደሚሆኑ በግምገማችን ላይ ሀሳብ ቀረበ። በዚህ ስብሰባ መጀመሪያ የተናገረው መድህን ነበር ሲናገር እያለቀሰና እንባውን በመሃረሙ እየጠረገ “እኛ የህ.ው.ሓ.ት አባላት በድርቅ ለተጠቃው የትግራይ ሕብረተስብ የመጣ እርዳታ ህዝባችን በአይናችን እያየነው በየመንገዱ ሲሞትና ቀባሪ አጥቶ በጅብ ሰውነቱ ተበጣጥስ መበላቱን እያየን፣ እናቶች ከህፃናት ልጃቻቸው ተለይትው ሞተው ህፃናት የሟች እናቶቻቸውን ጡት ነክሰው እነሱም በበኩላቸው ሞተው፤ አዋቂዎች አጥንት በስጋ ቆዳቸው ተጣብቀው የሚረዳቸው አጥተው ያለቁ፤ ወደ ሱዳን አጓጓዘን 10ኪሎ ጥሬ በቆላና ባቄላ እያደልን የራሳችን ህዝብ ለሞት አሳልፈን ሰጥተን፤ በህዝቡ ላይ ግፍ በመፈፀም መላውን የትግራይን ዜጋ አሳልፈን ሰጠነው። ይህ ለማ.ሌ.ሊ.ት ቀይ ስራዊት ተብሎ የተከማቸው ክምር ቀደም ብለን ለተጠቃው ህዝባችን ብንሰጠው ኑሮ ምስጋናም ምርቃትም እናገኝ ነበር። እዚሁ ደረጃ ያደረሰንን ህዝብ ከዳነው” እያለ ንግግሩን በለቅሶ አጠናቀቀው ቀጥሎ የመድህን ሃስብ በመደገፍ መዝገብ በበኩሉ ተናገረ።ብዙ ከተናገር በኋላ ተጨማሪ ብዩ እኔ የመዝገበንና የመድህን ሃሳብ በመደገፍ የማጠናከሪያ ሀሳቤን ስጨርስ  መድህን እንደገና በመቀጠል የህወሓት መሪዎችም የደረሰውን የህዝብ  መቅሰፍት

አይተውታል። ስለዚህ እኛ ሁላችን ህዝብ የኪዳን በችግር ጊዜ አናውቅህም ብለን የጣልነው የህዝብ ከሃዲዎች ነን ብሎ አቆመ።

የዚህ ስብሰባ ሪፓርት ሕቡር ገ/ኪዳን ለስብሃትና ለመለስ አቀረበላቸው። ሳይውል ሳያድር መድህን፣ መዝገበ፣ ገብረመድህን፤ በያንና ያይኔ ከኮምሽኑ ሥራችን እንድናቆም ተወስኖ ለአራታችን ህቡር በብጣሽ ወረቀት አስታወቀን። በዚሁ በእኛ ምትክ ሌሎች ተተኩ ስንት እንደተበላሸ ባናውቅም በየበረሃው የተከመሩ ክምሮች ግን በብዛት የተበላሹ መሆናቸው እናውቃለን።

በመጀመሪያው የድርቁ ጊዜ ወደ ሱዳን አንሄድም ብለው ወደ ጎንደር፣ ወሎ፣ አዲስ አበባ፣ ባህርዳርና ወደ ቀሪዎቹ የሀገራችን ክፍሎች የሄዱት ወደ ግማሽ ሚሊዮን ቁጥር ያለው ሕዝብ በደረሰበት ቦታ ሁሉ ኢትዮጵያዊ ወገኑ ተቀብሎ አስተናገደው፣ ልብስ ለሌለው የራሱን አውልቆ ገመነውን ሸፈነ፣ የተራበውን አበላ፤ መጠለያ ያጣውን ከራሱ ቤት እንዲኖር አድርጎ ከእርዳታ አስተባባርዎች አገናኝቶ ተጎጅው እርዳታውን እየተቀበለ ህብረተሰቡም ሙሉ ሕክምና እያገኙ በሃጋራቸው ምድር ቆዩ። ዝናብ ሲዘንብ ተመልሰው ወደ ትግራይ ቀያቸው ገቡ። ባረፉበት ትውልድ ቀበሌዎች ሁሉ ወገናቸውና ደማቸው ኢትዮጵያዊ ያደረገላቸውን መጠነ ሰፊ እርዳታ በደስታና ትዝታ በሞላበት አንደበት ያወጉ ጀመር ። የዚሁ ወሬ በህዝቡ ሁሉ ስለደረሰ ወንጀለኛው የወያኔ አመራር ተበሳጭቶ ወሬው ደግሞ እንዳይነሳ ለህዝብ ግንኙነት አመራር አስተላልፎ ነበር፤ ግን ስሚ አላገኘም። እውነታው አሁንም ቋሚ ነው።

## የደጀና ኑሮ

ቀደም ብየ እንደጠቀስኩት የህ.ወ.ሓ.ት ማ.ሌ.ሊ.ት ፓሊት ቢሮ ደጀና እንደተሰበሰበ አይተናል። በዚሁም ወታደራዊ ማስልጠኛ በየሁለት ወሩ ከ10,000 በላይ እያሰለጠነ የሚያመጣ ትምህርት ቤት፤ የወያኔ ትልቁ ሆስፒታል፤ የትራንስፓት ጽ/ቤት፤ ማህበረ ኢኮኖሚ፤ ስንቅና ንብረት አከፋፋይ ከደጀና እስከ ክሳድ ግመል እንደዚሁም እስከ ፀገዴ ቆላ በብዙ ሽህ የሚቆጠር ታጋይ ይገኛል። እድሜ ለድርቅ ኑሮው የተንበሸበሸ ሆነ፣ እየበላ እየጠገበ መኖር ጀመረ፤ ችግር የሚባል ነገር ተረሳ፤ ሴት ለሚያስፈልገው ሴት አለ። ሲቷም የመረጠችውን እንደዚሁ ታገኝ ጀመር። በየአካባቢው፤ በየክፍሉ ያሉ ታጋዮች በየሁለት ሳምንቱ ጠላ እየተጠመቀ ይጠጣል፤ ማታ ማታ ጭፈራና ዳንስ ነው።

## የአመራሩ የኑሮ ለውጥ

ቀደም ሲል ደጀና ውስጥ ሆኖ ልዩ ስሙ ክሳድ ግመል የሚባል ቦታ የድርጅቱ ጽ/ቤት ነበር፡ ነገር ግን አንድ ጊዜ ደርግ በአውሮፕላን ስለደበደበውና ገላጣ ስለሆነ ወደ ደጀና እንዲዛወር ተደረገ። የአሁኑ ቦታ ትልልቅ ዋሻዎች አሉት ለአውሮፕላንም ጥቃት የተጋለጥ አይደለም። አሁን ጽህፈት ቤቱ በሰው ኃይልም በሚገባ ተደራጀ። ፕሮፓጋንዳ ቢሮ መለስ ዜናዊ፤ ስብሀት ነጋ፤አባይ ፀሃዬ እና አለምስገድ ገ/ አምላክ ፤ ወታደራዊ ቢሮ ስዬ አብረሃ እና አርከበ እቁባይ፤ማህበራዊና ኢኮኖሚ ቢሮ ገብሩ አስራት፤ ህዝብ ግንኙነት ቢሮ ተወልደ፤ ሓለዋ ወያነ ጽ/ቤት ከፕሮፓጋንዳ ስር ሆኖ ክንፈ ገ/መድህንና ብስራት አማረ ሆነው ተመድበዋል። በተለይ ስብሃት ነጋ፤አርከበ እቁባይ ፡ኤልሳ አሰፋሃ የምትባል ኤርትራዊት የፃድቃን ገብረትንሳይ ሚስት ባለችበት ተነጋግረው ፓሊት ቢሮው ልዩ እንክብካቤ እንደሚያስፈልገው ታምኖበት በየወሩ ብር 50,000 በገንዘብ ሃላፊ ገ/መድህን አማካኝነት እየተፈቀደ ለኤልሳ አስፍሃ እንዲሰጥ ተወሰነ የማ/ኢኮኖሚው ሃላፊ ገብሩ አስራት ይህን አዲስ እቅድ አያውቅም። ትእዛዙ እንደደረሰኝ ጉዳዩን አለቃዬ በመሆኑ አሳወኩት፡ እርሱም የሚፈልጉትን አድርግላቸው ብሎኝ በየወሩ ብር 50,000 ለኤልሳ አስፍሃ ወጭ እያደረግሁ እሰጣት ነበር።

በመካከሉ ስብሃት ነጋ በየቦታው እየዞረ ለፓሊት ቢሮ አባላት ልዩ እንክብካቤ እንዲደረግ ስለተወሰነ የሚደረግላችሁን ተቀበሉ አላቸው። ተወልደ ወ/ማርያም፤ ስየ አብረሃ እና ገብሩ አስራት ግን ይህን አይነት ልዩ ቅምጥል አያስፈልገንም አንቀበልም አሉት። ሌሎቹ በውሳኔው መሰረት ልዩ እንክብካቤው ልዩ ኑሮ ከነሚስቶቻቸው በኤልሳ መሪነት ቀጠለ። ከዚያማ የነጭ ጤፍ እንጀራ፤ ሙክት፤ ቅቤ ማር ልዩ ልዩ የአትክልት ፍራፍሬ ከሱዳን ዊስኪ ቢራ ኮኛክ ነጭ አረቂ በኮንትሮባንድ ከየቦታው እየተገዛ ቀጠለ። መኝታ አልጋዎች ሳይቀሩ ፍራሽ ብርድ ልብስ አንሶላም ሳይቀር ተደምሮ አራት ሴቶች ከሱዳን ተመርጠው ለነመለስ ምግብ አዘጋጅ ተቀጠሩ።በዚህ ብቻ ሳያቆሙ ሁሉም የፓሊት ቢሮ አባላት በየወሩ ብር 1000 ሺህ የኪስ ገንዘብ እንዲከፈላቸው በነስብሃት የተደነገገ ሕግ ወጣ።

የታዘዘውን የኪስ ገንዘብ የሚቀበሉ 1 መለስ ዜናዊ 2 ስብሃት ነጋ 3 አባይ ፀሀዬ 4 አውአሎም ወልዱ 5 አረጋሽ አዳነ 6 አርከበ ዕቁባይ 7 ስዩም መስፍን 8 ፃድቃን ገ/ረንሳይ ሲሆኑ 1. ገብረ አስራት 2. ስዬ አብረሃ 3 ተወልደ ወ/ማረያም አንፈልግም ኣንቀበልም በለው ተቃወሙ፤ ሰሚ ግን አላገኙም።

ለማጠቃለል ያህል በድርቅ ለተጠቃው ለትግራይ ህዝብ የመጣው እርዳታ የህ.ወ.ሓ.ት መሪዎች እንዴት እንደዘረፉትና ዘረፈው ለግል ጥቅማቸው እንዳዋሉት በመጠኑም ቢሆን ያዩሁትን ሁሉ ምስክርነቴን አስፍሬአለሁ። የህ.ወ.ሓ.ት አመራር ጠቅላላ የትግራይ ህብረተስብ  በድርቅ እንደቅጠል በየቦታው እየረገፈ ህፃን እናት ሽማግሌ አባት ወ.ዘ.ተ በየመንገድ ጥላ ስር ቀባሪ አጥተው በጅብ አካላታቸው ተበጣጥሶ መበላቱን በአይናቸው እየተመለከቱ ለነብስ አድን የመጣውን እጅግ መጠነ ሰፊ እርዳታ ጉና በሚል ንግድ ድርጅት አቋቁመው በሱዳን አሽጋጋሪነት ለአረብ ሀገሮች እርዳታውን መሸጣቸውንና ከባንድ ኤድ የተገኘውን $100 ሚሊዮን ዶላርም ጨምረው በአውሮፓና በአሜሪካ ባንኮች በየራሳቸው ባንክ አካውንት ማዛወራቸውን። በተለያዩ ሀገራትም ምርጥ ቤቶች አስገዝተው ኪራይ ገቢ ቋሚ ገንዘብ መሰብሰባቸውን፤ ለቀይ ሰራዊት የአምስት አመት ቀለብ የቋጠሩበት መሆኑን፡ ይህ ሁሉ ተግባራቸው የሚያረጋግጠው የህ.ወ.ሓ.ት.ማ.ሌ.ሊ.ት መሪዎች ጨካኞችና ፋሽሽት መሆናቸው ነው።

ከዚህ በተጨማሪ የህ.ወ.ሓ.ት.ማ.ሌ.ሊ.ት መሪዎች በመለስ ዜናዊና በስብሃት ነጋ መሃንዲስነት የትግራይ ህዝብ በርሃብና በውሃ እጦት ብሎም በተለያዩ በሽታዎች እየረገፈ በህዝብ ስም የመጣውን እርዳታ  ነጥቀው ሰባት ዙር የካድሬ ትምህርት ስልጠና ማስፈጸሚያ ተጠቅመውበታል። በዚህ ብቻም አላበቁም። የማርክስ ሌኒናዊ ሊግ ትግራይ ፓርቲ ምስረታ በየትም አለም ተወዳደሪ የማይገኝለት በከፍተኛ የገንዘብ ወጪ በወርዒ አዳራሽ አሰርተው ጉባኤ በማካሄድ እነ መለስ ዜናዊ በቀይ ጨርቅ የተጠቀለለ አርማና ጉንጉን አበባ ተሸለሙበት። ይህን ሁሉ ማን ይናገር የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ እንደሚባለው ሁሉውን የጥፋት ድርጊት በዝርዝርና በነቂስ ህዝብ እንዲያወቀው ካሁን ቀደም አድርጌአልሁ አሁንም ይኸው የትግራይ ህብረተሰብ በድርቅ አስቃቂ ሁኔታ በየቦታው እየወደቀ በህዝብ ስም የመጣው መጠነ ስፊ እርዳታ በነመለስ ዜናዊ እጅ ውስጥ ገብቶ ለግል ጥቅማቸው ዋለ። ተጠቀሙበት። አራት ሚሊዮን ህዝብ በእነዚህ ይሉኝታ ቢሶችና ሆድ አደሮች ንብረቱ ተነጥቆ ለሰቆቃ ለቸነፈር ለአስከፊ ሞት ዳረጉት።

የወያኔ መሪዎች ከ1977 ዓ.ም እስከ 1981 ዓ.ም የፈፀሙትን መጠነ ሰፊ ወንጀልና ክህደት በትክክል አስቀምጨአለሁ፡ከዚህ በተረፈ ማንም የትግራይ ተወላጅ የተፈፀመው ግፍ አይቶና አውቆ በእውን የተወለደበት አካባቢ ግፍና ሰቆቃ ይሰማኛል ይቆረቁረኛል የሚል ከሆነና በአሁኑ ወቅት ከትግራይ አልፈው በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሚፈጸሙትን ሰቆቃ እና በተለይ ዛሬ ድግሞ እነመለስ በትግራይ ላይ የፈጸሙትን ደባ ሸፍነው ለትግራይ ሕዝብ እንደቆሙ በማስመሰል በስሙ አሁንም ሲነግዱበት ይሰማሉ። በመሆኑም በየወጭ ሃገር ካድሬና ደጋፊ የሆንክ ሁሉ ሁኔታውን ተገንዝበህ ከቀሪው ኢትዮጵያዊ ወገንህ ጎን እንደምትሰለፍ ጥርጥር የለኝ። በአገር ቤት የሚገኘውና ታፍኖ የተያዘው የትግራይ ህዝብ በቆራጥነት ትግሉን ከሃገሪቱ ህዝብ ጋር እንዲያቀናጅም ጥሪየን አቀርባለሁ። አቅራቢ የድሮው የህ.ወ.ሓ.ት ማሌሊት የፋይናንስ ሃላፊ ገ/መድህን አርአያ ነኝ።

www.ethiomedia.com – a website of alternative news and views
(TPLF is a mercenary-controlled group that cannot be reformed. Like apartheid, it should be dismantled)